የሐኪም ትእዛዝ የሚያስፈልጋቸውና የሐኪም ትእዛዝ የማያስፈልጋቸው መድሀኒቶች

- የቤተሰብዎ ሐኪም (GP) ወይም ደግሞ ስፔሻሊስት ለእርስዎ የሚሆን መድሀኒት በጽሁፍ ሊያዝዝ ይችላል
- ይህን የሐኪምዎን የጽሑፍ ትእዛዝ ይዘው ወደ ኬሚስት/ፋርማሲ መሄድ አለብዎት
- ፋርማሲስቱ ደግሞ መድሀኒቱን በማየት ስንት መክፈል እንዳለብዎት ይነግርዎታል፤ እንዲሁም መድሀኒቱ እንዴት መውሰድ እንዳለብዎት እና የሚያስከትለው ሳእቤን ካለ ደግሞ ይገልጸልዎታል
- አንዳንድ ኪኒኖች፣ ክሬም እና ፈሳሽ የሆኑ መድሀኒቶች የሐኪም የጽሑፍ ትእዛዝ ሳያስፈልግዎት መግዛት ይችላሉ። የሐኪም ትእዛዝ ለማያስፈልጋቸው መድሀኒቶች በተመለከተ ከመንግስት የሚሰጥ ክፍያ ወይም ቅናሽ የለም።

በሐኪም ለታዘዙ መድሀኒቶች መክፈል

- የሐኪሙ የጽሑፍ ትእዛዝ ይዘው ወደ ኬሚስት/ ፋርማሲስት በሚሄዱበት ጊዜ የመዲኬር ካርድ፣ የጤና እንክብካቤ ካርድ ወይም የጥሮታ አበል ካርድ ይዘው ከሄዱ የመድሀኒቱ ዋጋ ሊቀንስልዎት ይችላል
- ከፌዴራል መንግስት Pharmaceutical Benefits Scheme (PBS) በታች የተዘረዘሩት መድሀኒቶች ዋጋቸው ይቀንሳል።
- መድሀኒቶቹ የPBS ቅናች ዋጋ የሚያገኙ ከሆነ በሀኪም የታዘዙ መሆን አለባቸው፤ ነገር ግን ሁሉም የመድሀኒት ዓይነቶች በዚህ ክፍል ይገባሉ ማለት አይደለም። ሐኪምዎ በPBS ዝርዝር ውስጥ የሌለ ወይም ያልገባ መድሀኒት ካዘዝልዎት ሙሉ ዋጋ እንዲከፍሉ ይጠየቃሉ።
- የጤና እንክብካቤ ካርድ ካልዎት ለPBS መድሀኒት የሚከፍሉት ከፍተኛ ዋጋ፣ ከ$4.90 የማይበዛ ነው (ከጥር1፣ 2007)
- የመዲኬር ካርድ ካልዎት፣ ለPBS መድሀኒት የሚከፍሉት ከፍተኛ ዋጋ፣ ከ$30.70 የማይበዛ ነው (ከጥር1፣ 2007)
- እነዚህ ዋጋዎች በጥር 1 ቀን ላይ በየዓመቱ የሚስተካከሉ ናቸው
- የቤተሰብዎ አባላት በአንድ ዓመት ውስጥ ብዙ መድሀኒት የሚያስፈልጋቸው ከሆነ፣ ለብዙ ዓይነት መድሀኒት በሚከፍሉበት ጊዜ በቅናሽ ዋጋ እንዲሰጥዎት ስለ 'Safety Net' የሚባለው ሌላ ዓይነት ድጋፍ ፋርማሲስቱን ይጠይቁ። ፋርማሲስቱ ደግሞ ለዚህ ዓይነት ፖሊሲ እንዴት እንደሚያመለክቱ ያሳይዎታል።

ፋርማሲስቱ፣ ዋጋው ቅናሽ የሆነ የጀነሪክ ዓይነት መድሀኒት ይፈልጉ እንደሆነ ሊጠይቅዎት ይችላል። ብዙ መድሀኒቶች ዓይነታቸው ከአንድ በላይ ናቸው እና ዋጋቸው ደግሞ እንደ ዓይነታቸው ሊለያይ ይችላል። ጀነሪክ መድሀኒቶች አንድ ዓይነት መጠንና ይዘታ አላቸው፣ እንዲሁም አንድ ዓይነት ሀይል አላቸው። እንዲሁም ከነዛ ውድ የሆኑ መድሀኒቶች ጋር አንድ ዓይነት ውጤት የሚያስገኙ መሆናቸውን በጥናት ተረጋግጠዋል።

መድሀኒቶች መውሰድ

- በመድሀኒቱ ወረቀት ላይ የተጻፉ የመድሀኒቱ አጠቃቀም መመርያዎች አሉ። መመርያው ግልጽ ካልሆነ፣ ፋርማሲስቱ በቃል እንዲያብራርልዎት ይጠይቁት። ቀጥሎ የተዘረዘሩት ነገሮች በጥንቃቄ መከተሎት ያረጋግጡ ፣
  - ለሌላ ሰው የታዘዘ መድሀኒት መውሰድ የለብዎትም
  - ረጅም ጊዜ ያለገ ወይም ቀኑ ያለፈ መድሀኒት መውሰድ የለብዎትም
  - መድሀኒቶቹ ሕጻናት በማይደርሱበት ቦታ ያስቀምጡ
  - ሌላ የተከሰተ የማይገባ ጉዳት ካዩ እንደገና ወደ ሐኪምዎ በመሄድ ይንገሩት
  - ለእርስዎ የታዘዘ መድሀኒት ለሌላ ሰው በውጭ አገር የሚኖር ዘመድዎ ቢሆንም መስጠት የለብዎትም
  - መድሀኒቱ በሚወስዱበት ጊዜ የሚያጋጥም ችግር ካለ ወይም ደግሞ በመርሳት መድሀኒቱ ሳይወስዱ ከቀሩ፣ ፋርማሲስቱን ወይም ዶክቶሩን ያሳውቁት
  - መድሀኒቶቹ ለማስቀመጥ ምን እንደሚያስፈልግ መረዳት አለብዎት - ለምሳሌ አንዳንድ መድሀኒቶች በፍርጅ ውስጥ ማስቀመጥ ሲኖርብዎት አንዳንዶቹ ግን በፍርጅ ውስጥ ማስቀመጥ የለብዎትም
  - ሌላ መድሀኒት እየወሰዱ ከሆነ፣ አዲስ መድሀኒት በሚወስዱበት ጊዜ፣ ከዛ መድሀኒት ጋር የሚስማማ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ ፋርማሲስቱን ወይም ዶክቶሩን ይጠይቁት።

መድሀኒቶች ሁሉ ጊዜ በሐኪም የጽሁፍ ትእዛዝ ብቻ ይገኛሉ ማለት አይደለም